በትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት ታተመ



ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዮሐንስ እጅ እንደተጠመቀ ።

# ጥምቀተ ክርስቶስ

## በ ዮ ር ዳ ኖ ስ

# EPIPHANY

Jan. 19, 1974


- የምወደው ልጄ ይህ ነው ።
- የብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክ የልደት መልእክት
- ጥምቀተ ክርስቶስ በዮርዳኖስ ፣
- ሥርዓተ ጥምቀት
- የመጀመሪያው ተአምር ፣
- የፓትርያርክ ፒሜን ጉብኝት ፣
- የሩሲያኖች የኢትዮጵያን ታሪክ መተርጐም ፣
- የኢትዮጵያና የሩሲያ መንፈሳዊ ግንኙነት አጀማመር ፣

---

- *Epiphany*
- *The first visit of Patriarch Pimen in Ethiopia*
- *Soviet - Ethiopian Relationship*



## ዜና ቤተ ክርስቲያን

ዘኢትዮጵያ ።


ለ፲፱፻፷፮ ዓ/ ም በዓለ ጥምቀት በተለይ የተዘጋጀ መጽሔት ።

www.ethiopianorthodox.org

ይህ መጽሔት ለ፲፱፻፸፯ ዓ ም በዓለ ጥምቀት ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መንበረ ፓትርያርክ የስብከተ ወንጌልና ማስታወቂያ መምሪያ ተዘጋጀ ።

የመጽሔቱ ዋና አዘጋጅ ፡ ወልደ ሩፋኤል ፈታሒ

ም/አዘጋጅ አፈወርቅ አሰግድ ።

EDITOR IN CHIEF Wolde Ruffael Fetahi
DEPUTY EDITOR Afework Asseged

አዲስ አበባ

ጥር ፲፩ ቀን ፲፱፻፸፯ ዓ ም

www.ethiopianorthodox.org



ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ የኢትዮጵያ ፓትርያርክ ።
*His Holiness Abune Theophlos Patriarch of Ethiopia*

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

ርእሰ አንቀጽ

# የምወደው ልጄ ይህ ነው

ስለ ሰው ልጆች ድኅነት ስለ ሰው ልጆች ነፃነት ሲል ወርዶ መድኅን የሆነን ክርስቶስ ነው ።

እኛን ለማዳንና በደሙ ሊከፍለን ስለ እኛ ያለፈ መድኀኒታችን ክርስቶስ በእኛው መካከል በተራ ሰውነት ተወለደ ቀስ በቀስም አደገ ።

በጥምቀት ልጅነትን አግኝተን ዳግመኛ በመንፈስ እንወለድ ዘንድ አስፈላጊ መሆኑን ለማስተማር ሲል በዮሐንስ እጅ በዮርዳኖስ ወንዝ ተጠመቀ ።

በእዚያን ጊዜ የተገለጸው ምሥጢር ረቀቅ ያለና ለሰው ልጆችም ከእግዚአብሔር ዘንድ ልጅነትን ማግኘት እንዴት እንደሚቻል የተማርንበት ያወቅንበት የተረዳንበት ጊዜ ነው ።

ቀደም ሲል «የጌታን መንገድ አዘጋጁ ጥርጊያውንም አቅኑ» እያለ በምድር በዳ የሚጮኽ ድምጽ የክርስቶስን ጌትነት የክርስቶስን አምላክነት የክርስቶስን ልዕልና ሲያስተምረንና ሲያስረዳ ቆይቷል ሜቴ ፡ ምዕ ፡ ፫ ፡ ቍ፫ ።

በነቢያት ቀደም ሲል የተነገረውን ትንቢት ለመፈጸም ጊዜው ሲደርስ ዮሐንስ መንግሥተ ሰማያት ቀርባለችና ንስሐ ግቡ እያለ በይሁዳ ምድር ሁሉ እየተዘዋወረ የእግዚአብሔር መንግሥት ወደ ሰው ልጆች መምጣቷን ይሰብክ ያስተምር ያውጅ ነበር ።

ዮሐንስም በውኃ እየጠመቀ የክርስቶስን አምላክነት በማስተማር «እኔ በውኃ አጠምቃችኋለሁ ከእኔ በኋላ የሚመጣው ግን ከእኔ ይልቅ ይበረታል በመንፈስ ቅዱስም በእሳት ያጠምቃችኋል«በማለት ክርስቶስ ፈጣሪ መሆኑን በጉላና በተረዳ መልክ መስክሯል ።

በዚያን ጊዜ ኢየሱስ ከገሊላ ወደ ዮርዳኖስ መጥቶ በዮሐንስ እጅ ከተጠመቀ በኋላ ከተጠመቀበት ወሀ ውስጥ ብቅ ሲል የሦስትነትና የአንድነት ምሥጢር ተገልጿል ።

የአብ የባሕርይ የአባቱ ድምፅም በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው፥ ሲል ተሰምቷል መንፈስ ቅዱስም በአምሳለ ርግብ ወርዶ ወልድም በእዚያን ጊዜ በዮርዳኖስ ወንዝ በሥጋ ተዋህዶ ሲጠመቅ ታይቷል ።

በክርስቶስ ጥምቀት ሰማያት ተከፍተው ይህን የመሰለ ታላቅና አስደናቂ የሆነ አምላካዊ ተአምራት የተገለጸበት ዕለት ነው ይህን ከፍተኛ የረቀቀ ምሥጢር ያዘለውን በዓል የምናከብረው ከእዚህ በላይ በገለጽነው ዓይነት የተፈጸመ በመሆኑ በአንክሮና ከእግዚአብሔር ጋር በጥምቀት የተዋሃድንበትን ጊዜ በማሰብ ነው ።

ቤተ ክርስቲያናችንም በየዓመቱ የጌታችንን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን በዓል ጥምቀት የምታከብረው በደመቀ መንፈሳዊ ሥነ ሥርዓት ሲሆን በተለይ ካህናቱና ምእመናኑ በጥምቀተ ባሕሩ በሚገኙት ታቦታት ዘንድ ሔዶ በማደር ስብሐተ እግዚአብሔር በማድረስ ያከብሩታል ።

ወንዱም ሴቱም ስለ ክርስቶስ ፍቅር ያላቸውን ውዴታ በየቋንቋቸው በማዜም ታቦታቱን እያጀቡ ደስታቸውን ሲገልጹ መመልከት አንድ የተለየ የመንፈስ ደስታ ነው ።

ዜና ቤተ ክርስቲያን ጋዜጣችን ይህንኑ በዓል ምክንያት በማድረግ እንኳን ለብርሃን ጥምቀቱ በሰላም አደረሳችሁ በማለት በዓሉ የፍሥሐ የሰላምና የፀጥታ ይሆንላችሁ ዘንድ ምኞቱን ይገልጻል ።

www.ethiopianorthodox.org

# የብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክ
# የልደት መልእክት

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን፡
ሰላም በምድር ፡

ስብሐት ለእግዚአብሔር በሰማያት ወሰላም በምድር ሥምረቱ ለሰብእ ሉቃ ፡ ፪፡፲፬፡ ምስጋና በአርያም፡ ሰላም በምድር ፡ ፍቅር ለሰው ይሁን ።

ይህ ቃል ከሺህ ዘጠኝ መቶዓመት በፊት የተነገረ ቢሆንም በቃሉ መሠረትነት ብዙ የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት የራቀውን የረቀቀውን የሃይማኖት ምሥጢር ለመግለጥ ብዙ ጽፈውበታል ፡ ብዙ ተናግረውበታል ። ዛሬ ያሉትም በመሠረትነቱ አጽንተው ሐሳባ ቸውን በመግለጽ ላይ ናቸው ፡

ይህ ቃል መልእክትም ፡ ሰውም ሐሳባቸውን በምስጋና፡በማስተማር በጽሕፈት ለመግለጽ ቢቀዱት ፡ የማያልቅ የመንፈስ ምንጭ ነው ፡

ጌታችን የተጠማ ቢኖር ወደኔ ይምጣና ይጠጣ መጽሐፍ እንደ ተናገረ የሕይወት ውኃ ከሱ ሲፈልቅ ሲመነጭ ይኖራል ስለአለ ወደ እግዚአብሔር በሃይማኖት የቀረቡ ቃሉን የተቀበሉ ሁሉ ይህ መን ፈሳዊ ምንጭ ከነሱ ፈልቆ ወደ ዓለም ዘልቆ ዘር ፡ ተክል የማይገኝ ባቸውን በረሃዎች ማለት ዘርዐ ሃይማኖት ፡ ፍሬ ምግባር የማይገኝባቸ ውን ሁሉ ሊያለመልማቸው የሕይወት ባለቤቶች ሊያደርጋቸው ይችላል

ዛሬም በዚህ ቃል መሠረትነት የእግዚአብሔርን ቸርነት እንናገ ራለን ፤ እግዚአብሔር ሰው መሆኑ ሳይታሰብ በድንገት ፡ ባጋጣሚ ወይም ለማይጠቅም ነገር አይደለም ። ሁሉ በሚቻለው በእግዚአብ ሔር ሕሊና ታስቦ የተፈጸመሲሆን ጥቅሙም በኃጢአት ተሸንፎ ከክ ብሩ ለተዋረደው ከደገኛይቱ ርስቱ ለወጣው የእግዚአብሔር ቤተ ሰብ በመሆን ፈንታ ለሰይጣንና ለፈቃዱ ታዛዥና አገልጋይ ፡ ምር ኮኛም ለሆነው ለሰው ሕይወት ነው ።

በኃጢአት ምክንያት የሰው ልጅ ኑሮ ከክብር ወደ ሐሣር፡ ከብርታት ወደ ድካም ፤ ከጤና ወደ ሕማም ፡ ከሕይወት ወደ ሞት ስለ ተለወጠ



ሰላም የጐደለው ብቻ ሳይሆን ጨርሶ የሌለውም ሆነ ።

በዚህ ምክንያት የሰው ልጅ ብዛት ቍጥር ገና የአሥር ቤት እንኳ ሳይሞላ ቃየል ወንድሙን አቤልን ገደለውና የሰው ልጅ የኑሮ በር በደም ተከፈተ ፡ ከመጀመሪያው እስከ ዛሬ ዓለም የጨበጠችው የወርቅ ጽዋው ደም እንደተሞላ ነው ፤ እግዚአብሔርም ከአንዱ ወደ ሌላው ሲያቃዳውና ሲያገለ ባብጠው ስለሚኖር ከአዳም ልጆች ራስ አልወረደም ።

እንግዲህ ልዑል እግዚአብሔር ሰው የሆነው ፤ ሥጋ የለበሰው በግብረ መንፈስ ቅዱስ ከድንግል የተወለደው ፤ በበረት የተጣለ ፤ በጨርቅ የተጠቀለለ እሳዛኙን የሰውን ልጅ ሕይወት ለማደስ ፤ ለመቀ ደስ ከደም ወደ ሰላም ለመመለስ ነው ።

ሁለንተናው በደም የተበከለ ልብስ በእሳት ለመቃጠል ካልሆነ በቀር ለምንም እንደማይጠቅም ሰውም እንዲሁ ሆኖ ነበር ፤ ነገር ግን ያመነበት ሁሉ እንዲድን አንድ እንኳን እንዳይጠፋ ሕፃን ተወለደልን ወልድ ቢዛ ኾኖ ተሰጠን፤ሥልጣን የባሕርዩ ነው ፤ ያሰበውን የማይ ለውጥ ጌትነት ገንዘቡ የሆነ የሕይወት ባለቤት ነው ስሙም የሰላም አለቃ ይባላል፡ ስለዚህ ይህ የሰላም ንጉሥ በተወለደ ጊዜ ምስጋና በአርያም ፤ ሰላም በምድር ፤ ፍቅር ለሰው የሚል የማይመረመር ጣዕም የሞላበት የዜማ ምስጋና ከመላእክት አንደበት ተሰማ ።

እነዚህን በዜማ የተገለጡትን ቃላት አተኩረን ስንመለከታቸው ብዙ ሐሳብ ያቀርቡልናል ፤ ግን ከብዙ ጥቂቱን መመልከት ይቻላል ፤ «ምስጋና በአርያም» የሚለው ቃል በሰማያዊው ዓለምና በሰማያው ያን ነዋሪዎች ዘንድ የጐደለ የሚጐድል ነገር አለመኖሩን ያሳየናል ።

ስለዚህ ምስጋና በአርያም ሞልቶ ይኖራል ፤ ሰላም በምድር የሚ ለው ቃልም ምድር ምን ጊዜም በሰላም ፤ በፀጥታ አለመኖሯን ያሳ ያል ፤ የጥንተ ፍጥረትን ዜና ስንመለከተውም እንኳ ምድር ባዶዋን ነበረች ይልና ነፋስ ውኃው ላይ ይዋኝ ነበረ ጨለማም ሸፍኖት ነበረ ሲል በላይዋ የነበረው በነፋስ ኃይል ሲናወጥ ፤ ሲበጠበጥ እንደ ነበረ ያሳያል ፤ ኋላም ውኃው በከፊል ምድርን ሲለቃትና በለቀቀው ውኃ ፈንታ ሰው ተተክቶ ኑሮውን ሲጀምር ከውኃ ምግብነት ያገ ኘው ሁከት ለምድር ዕረፍት ስላልሰጣት ዓለም የሰላም መሆኑ ቀርቶ የሁብ የክርክር ዓለም ሆነ ፤ ሰው አብዝቶ ኃጢአት ሠራ ከጀመረው የኃጢአት ጉዞም መመለስ አልቻለም ፤ ወንድም በወንድሙ ላይ ቂም ያዘ ፤ የወንድሙን ደም ለማፍሰስ ሾተል መዘዘ ፤ ስለዚህ ሰላም ከም ድር ሸሸ ፤ ጠፋ ፤ በላይዋም ጽላሎተ ሞት ተደፋ ፤ ይህንን ከባድ የጭ



www.ethiopianorthodox.org

ለማ ኃይል ሽሮ የሰውን ሁከት ጸጥ ለማድረግና ሰላምን ለማስገኘት አንድ ታላቅ ኃይል ያስፈልጋል ፤ ይኸውም ፍቅር ነው ።

ስለዚህ ሰላም በምድር የሚለውን ቃል ፍቅር ለሰው የሚል ቃል ተከትሎት እናያለን ጥላቻ በፍቅር ሲሻር ሰላም በዕርቅ ስለሚጀመር የሰው እርስ በርሱ መስማማት ለዓለም ሰላም መሠረቱ መሆኑ እውነት ነው ፤ ለዚህ ታላቅ ነገር የዓለሙን መድኅን የባሕርይ አምላክ ክርስቶስ በዳዊት አገር በቤተ ልሔም ተወለደ ። በሰውና በእግዚአብሔር መካከል የነበረው መገናኘትን ክልክሎ የነበረው ግምብ ተናደ ፤ ሰውና እግዚአብሔር ፊት ለፊት ተያዩ ፤ የልባቸውንም ቃል በቃል ተወያዩ ፤ ልዑል እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ሲጠሉት መውደድን አሳይቶ ሰላምን ፤ ፍቅርን ለዓለም ሰበከ ። በነቢይነት ወይም በሌላ ልዩ ልዩ ሥልጣን ወደ ዓለም የገቡ የሰው ልጆች ሁልጊዜ የኃይል በትር ስለሚመረኰዙ በምድር ላይ ሰላምን ማብቀል ፍቅርን መትከል አልተቻላቸውም ።

ሁሉ ሲቻለው ምንም ነገር ሳይጐድለው በደካማ ሰውነት የተገለጠው ኃያል አምላክ ግን ኃይልን በድካም ስለሻረው በምድር ላይ ሰላምን መዝራት ፍቅርን ማስፋፋት ተቻለው ፤ ሰው እርስ በርሱ ተስማምቶ ለመኖር የሚችልበት የአንድነት ፤ የስምምነት ኃይል የተገኘው ከርሱ ብቻ ነው ፤ ጌታችን በዚህ ዓለም ሲያስተምር በነበረበት ጊዜ ከሠራቸው ፤ ከተናገራቸው እንዳንዶቹን እንኳ ብንመለከት ፍቅርና ሰላም ሊኖሩ ፤ ሊስፋፉ የሚችሉበት መንገድ የትኛው እንደ ሆነ ልንረዳ እንችላለን ።

ልዑል አምላክ ትሑት ሥጋን በመዋሐድ በአጭር ቁመት በጠባብ ደረት ተወስኖ ተገኘ ፤ ድንግል እናቱ በበረት አስተኛችው በጨርቅ ጠቀለለችው ፤ አውራጣቱን አሠረችው ፤

በዮሐንስ እጅ በዮርዳኖስ ወንዝ ተጠመቀ፡ አርባ መዓልት አርባ ሌሊት ጦመ፤ በዚህም መለያየትን የወለደውን ሰላምን ያደፈረሰውን ፤መብልን ከነበረበት ቦታው ዝቅ ከማድረጉም በላይ ባ ይ ኖ ር ም እንደ ማይጎዳ አስረዳ ፤

ትዕቢት በትሕትና ንፍገት በምጽዋት ቢለወጥ ታላቅ ጥቅም እንደ ሚሰጥ ገለጠ ፤ ይህንንም በሥራ ፤ በቃል አስተማረ ፤

ዓለም ይህን ቢከተል ቂም ቢያርቅ፤ደም ቢያደርቅ እርስ በርሱ ቢደጋገፍ አንዱ አንዱን ባይጸየፍ የሌላው ችግር የራሱ መሆኑን ቢያውቅ እንደ ራሱ የወንድሙን መብት ቢጠብቅ ፤ ፍቅር ትጸናለች ፤ሰላም ትገኛለች ያን ጊዜ ከመላእክት ጋር ሰላም በምድር ፍቅር ለሰውብሎ



መዘመር ይችላል ፤ ምሥጋናም በሰማይ እንዳለ ሁሉ በምድርም ሊሟላ ይችላል ፤ የክርስቲያን ቤተ ሰብ ሁሉ የሰላሙ ንጉሥ የኢየሱስ ክርስቶስን ልደት ያከብራል ፤መታሰቢያውንም በየዓመቱ ያደርጋል ።

እኛም በዛሬይቱ ቀን በዓለ ልደቱን የምናከብረው በዚሁ መሠረት ነው ፤ ይሁን እንጂ እንስሳትእንኳ ጌታቸውን የሚያውቁ ፈቃዱን የሚፈጽሙ ስለሆነ ሰውም ጌታውን ፤ አምላኩን ለይቶ ማወቅ ፤ ፈቃዱንም መፈጸም ይገባዋል ። የእግዚአብሔር ፈቃድ የኛ ቅድስና ነው ፤ ይህም የሚገኘው በአንድነት ፤ በስምምነት ስንኖር ለተቸገረው ስናዝን ፤ ስንራራ ሃይማኖታችንን ስናጸና ፤ ምግባራችንን ስናስፋፋ ፤ እውነት መናገርን ስንከተል ፤ ተንኮልን መሥራትሲቀር ነው ።

ክርስቲያኖች ለሥጋዊ ፍትወትና ፍላጐት ተገቢዎች መሆንን ትተው ለመንፈሳዊ ፈቃድና ዓላማ ባለቤት ሲሆኑ ፤ ያን ጊዜ በበረት የተወለደውን አምላክ ፊት ለፊት ያዩታል ፤ ገንዘባቸውን ፤ በምጽዋት ፤ ቊርባናቸውን በመሥዋዕት ያቀርቡለታል ፤ በብርሃን ሃይማኖት ወደ እሱ ይመራሉ ከኖሎት ፤ ከመላእክት ጋራ ይዘምራሉ ፤ ከሰብአ ሰገል ጋራ ፍሬ ትሩፋት ይገብራሉ ፤ ይህ ተስፋ እንዳያልፈን ፤ ይህ ዕድል እንዳያመልጠን ትጥቃችን የጠበቀ ፤ መብራታችን የበራ መሆን አለበት ።

## ም እ መ ና ን ፤

እርስ በርሳችሁ ተዋደዱ ፤ በችግራችሁ ተረዳዱ ፤ እግዚአብሔርን ፍሩ ፤ ንጉሥንም አክብሩ ፤ የሰላም መድኅን ፤ የሰላም አምላክ ለእኛ ለሀገራችን ለንጉሠ ነገሥታችን ፤ ለሕዝባቸውና ለሠራዊታቸውም ወልድ ዋህድ በሚል እምነት ጸንታ ለምትኖረው ቤተ ክርስቲያናችንም በረከተ ልደቱን ይስጥ ። የልደቱን ክብረ በዓል ይባርክ አሜን ።



www.ethiopianorthodox.org

# ጥምቀተ ክርስቶስ በዮርዳኖስ

ጥምቀት የኃጢአትን ሥርየትየምንቀበልበት የመንፈስ ቅዱስንም ልጅነት የምናገኝበት የእግዚአብሔር ወዳጆች የምንሰኝበት ቅዱስ ሥርዓት ነው ። አዳምና ሔዋን እግዚአብሔር በመልኩና በምሳሌው ፈጥሮ በገነት አኖራቸው ። ከትእዛዙ እንዳይተላለፉም ቃሉን ቢጠብቁ በሕይወት እንደሚኖሩ ቢተላለፉ ደግሞ በሞት እንደሚቀጡ አስጠነቀቃቸው ።

ነገር ግን ሔዋን ከተከለከለው ዛፍ ፍሬውን ወስዳ በላች ፤ ለባልዋም አበላችው ። ወዲያውም እግዚአብሔር ሊጐበኛቸው ሲመጣ በፊቱ ሊቆሙ አልቻሉም ። እንዳይነኩ የታዘዙትን ተላልፈው በልተው ተገኝተዋልና ኃጢአታቸውን ተረድተው ከፊቱ ሸሹ እግዚአብሔርም በአድራጐታቸው አዝኖ ከገነት እንዲወጡና በወዛቸው እንጀራቸውን እንዲበሉ አዘዛቸው ።እነሱም ኃጢአታቸውን ተገንዝበው በንስሐ ስለ ተመለሱ አምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመን ሲፈጸም ከሰማየ ሰማያት ወርዶ ከእመቤታችን ድንግል ማርያም ተወልዶ እንደሚያድናቸው ተስፋ ሰጣቸው ።

ስለ ዚህ እግዚአብሔር የተናገረውን የማይረሳ የሰጠውን የማይነሳ አምላክ ስለሆነ የተናገረውን ቃል እስኪፈጽመው ድረስ በነቢያት እያናገረ ከትውልድ ወደ ትውልድ እያስተላለፈ አቆየው ። ዘመኑ በደረሰ ጊዜም ሰማይና ምድር የማይወስኑት አምላክ በአጭር ቁመት ፤ በጠባብ ደረት ተወስኖ በማኅፀነ ድንግል አደረ ። ባማረና በከበረ ሥፍራ ሳይሆንም በተናቀና በላሞች ግርግም በቤተ ልሔም ተወለደ ። ነገር ግን የሰማይና የምድር ገዥ መሆኑን የተረዱት መላእክት ከሰማየ ሰማያት ወርደው ክብር ለእግዚአብሔር በአርያም ሰላምም በምድር ለሰው ልጆች እያሉ ከሰዎች ጋር ሁነው ዘመሩለት ።

ሆኖም እንደአምላክነቱ መጠን ወዲያው ልደግ ሳይል እንደ እኛ በጥቂት በጥቂቱ አደገ ። በሠላሳ ዓመቱም በአገልጋዩ በዮሐንስ እጅ በፈለገ ዮርዳኖስ ተጠመቀ ። ይሁን እንጂ እውነተኛው ጥምቀት በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ እስከሚሰጠን ጊዜ ድረስ የጥምቀት ምሥጢር በብዙ ምሳሌዎች እንደተሠራ (እንደተፈጸመ) እንመለከታለን ።

ለምሳሌ በኖኅ ዘመን የነበሩት ሰዎች በኃጢአት ምክንያት ከገጸ ምድር እንደ ተደመሰሱና እውነተኛ ጻድቅ ሆኖ የተገኘውን ኖኅን ከነቤተ ሰዎቹ እንደ አዳነው እናውቃለን ። ስለዚህ ከዚህ አስደናቂ ተአምር የጥምቀትን ምሥጢር እንመረምራለን ። የኖኅ መርከብ በባሕር ላይ እየተንሣፈፈች ኖኅን ከነልጆቹ እንስሳት አራዊትን ፤ በየወገናቸው አድናለች ። ስለዚህ መርከብ የቤተ ክርስቲያን ባሕር የጥምቀት ፤ ኖኅና ቤተ ሰዎቹ የምእመናን ምሳሌዎች ናቸው በኖኅ ጊዜ በመርከብ ድኅነት እንደተገኘ ባሁኑ ጊዜ ደግሞ ድኅነት የሚገኘው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመሠረተልን ጥምቀት ነው ።

ሁለተኛ ምሳሌ ደግሞ እስራኤላውያን በግብፅ አገር ለ፬፻፴ ዘመንበእንግድነት ከኖሩ በኋላ በሙሴ መሪነት በእግዚአብሔር ቸርነት ባሕረ ኤርትራን ተሻግረው ቀን በደመና ሌት በብርሃን እሳት እየመራ የወሰዳቸው የጥምቀት ምሳሌ እንደ ነበር ሐዋርያው ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች በጻፈው መልእክቱ «ወንድሞች ሆይ ይህን ታውቁ ዘንድ እወዳለሁ ፤ አባቶቻችን ሁሉ ከደመና በታች ነበሩ ። ሁሉም በባሕር መካከል ተሻገሩ ። ሁሉም ሙሴን ይተባበሩ ዘንድ በደመናና በባሕር ተጠመቁ ። ሁሉም ያን መንፈሳዊ አለት ጠጥተዋልና ያም አለት ክርስቶስ ነበረ ብሎ አል» ፩ኛ/ቆሮ ፡ ፲ ፡ ፩—፵፱



ሶስተኛ ምሳሌ ደግሞ እግዚአብሔር ከአብርሃም ጋር የገባው ቃል ኪዳን ግዝረት እንደነበር ሲታወቅ ያ ግዝረት የጥምቀት ምሳሌ ሆኖ ሲሠራበት እስከ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዘመን ድረስ እንደ ነበረ እንረዳለን ። መጥምቁ ዮሐንስም የንስሐ ስብከት እየሰበከ ለኃጢአት ሥርየት በውሃ ያጠምቅ ነበር ። ነገር ግን ይህ ሁሉ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ለሚሰጠን የልጅነት ምሳሌ እንጂ እው ነ ተ ኛ ጥ ም ቀ ት አልነበረም ። በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ የተሰጠን ጥምቀት በውሃ ብቻ ሳይሆን ከውኃው ጋር በተዋሃደው በእግዚአብሔር ቃልና በመንፈስ ቅዱስ ነው ።

መጥምቁ ዮሐንስ ከጌታችን ጥምቀት በፊት የነበረው ሁሉ ለኃጢአት ሥርየት እንጂ የመንፈስ ቅዱስ ተሐድሶ እንደ ሌለበት ሲያስረዳ «እኔ ግን በውኃ አጠምቃችኋለሁ ። ነገር ግን የጫማውን ጠፍር መፍታት ከማይገባኝ ከእኔ የሚበረታ ይመጣል ። እርሱ በመንፈስ ቅዱስና በእሳት ያጠምቃችኋል ። ብሎ አል» ማቴ ፡ ፫ ፡ ፲፩ ። ሉቃ ፡ ፫ ፡ ፲፯ ።

ከዚህ በኋላ ሕዝቡም ሁሉ ተጠመቁ ። ጌታችንም በዮሐንስ ይጠመቅ ዘንድ ከገሊላ ወደ ዮርዳኖስ መጣ ። የዮርዳኖስ ወንዝ መነሻው ከአርሞንኤም ተራራ ሥር ሲሆን መድረሻውም የጨው ባሕር ነው ። ይህ ተራራ የሚገኘው በእስራኤል አገር በስተ ሰሜን ግዛት ነው ። የዮርዳኖስ ወንዝ በስተ ሰሜን ከፍ ብሎ በስተምራውና በስተቀኙ በኩል የአርሞንኤምና የሊባኖስ ተራራዎች ከበውት ይታያሉ ። ውበትና ድምቀትም ሰጥተውት ይኖራሉ ። የዮርዳኖስ ወንዝ ርዝመት ፫፻፳ ኪሎ ሜትርነው ።

ይህ ወንዝ ሶስት ሐይቆች ይገኙበታል እነርሱም ፩ኛ/ የሚሮሞ ውኃ ፪ኛ/ የገሊላ ባሕር ፫ኛ/ የጨው ባሕር ናቸው ። ወንዙ ከሰሜን ግዛት ተነሥቶ በነዚህ ሐይቆች መካከል አቋርጦ ወደ ደቡብ ይጓዛል ። ከጨው ባሕር ጋርም ይቀላቀላል ። እንግዲህ መጥምቁ ዮሐንስ ሕዝቡን ያጠምቅበት የነበረው የወንዙ አትጣጫ በገሊላ ባሕርና በጨው ባሕር መካከል ባለው አማካይ ሥፍራ ነው ። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም በዮሐንስ ይጠመቅ ዘንድ ከገሊላ ተነሥቶ ወደ ዚህ ሥፍራ እንደመጣ እንረዳለን ።

ጌታችን በዮሐንስ እጅ ይጠመቅ ዘንድ ከገሊላ ወደ ዮርዳኖስ የመጣበት ዋና ዓላማ ለትሕትና ፤ ለትምህርትና ለእኛ ምሳሌ እንዲሆን ነው።ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ይህንኑ አብነት ባያሳየን ኖሮ በመካከላችን ትሕትና ባልተገኘም ነበር ። ገዥዎችና ባለጸጎችም ካህናትና መምህራንን ወደ ቤታችን እየመጣችሁ አስተምሩን አጥምቁን እያሉ ማስገደዳቸውና ማስቸገራቸውን ባልተውም ነበር ስለዚህ ነው ዮሐንስ የጌታችንን ትሕትና በማድነቅ «እኔ በአንተ ልጠመቅ ያስፈልገኛል እንጂአንተ ወደ እኔ ትመጣለህን ? በማለት የተከራከረው ። መምህረ ትሕትናና የፍቅር መገኛ የሆነው አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ግን አሁንስ ተው እንዲህ ጽድቅን ሁሉ መፈጸም ይገባልና ሲል አስረድቶታል ። ወዲያውም ተያይዘው ወደ ወንዙ ወርደዋል ። ጆንደኔት እንደሚያጠምቀው ጠይቆ ከተረዳ በኋላም አጥምቆታል ።

ጌታችን ከውኃው ሲወጣም ዮሐንስ እነሆ ሰማያት ተከፈቱ የእግዚአብሔርንም መንፈስ እንደ ርግብ ሲወርድ በእርሱ ላይም ሲመጣ አየሁ እነሆም ድምፅ ከሰማያት መጥቶ በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው ። ሲል ሰማሁ ብሎ መስክሮለታል ። በዚህ ትምህርት ውስጥ የእግዚአብሔር አብን ወላዲነት የእግዚአብሔር ወልድን ተወላዲነት ፤ የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስንም ሠራፂነት በመገንዘብ ምሥጢረ ሥላሴን እንመረምራለን ። ማቴ ፡ ፫ ፡ ፲፫—፲፯ ። ማር ፡ ፩ ፡ ፱—፲፩ ። ሉቃ ፡ ፫ ፡ ፳፩ ፡ ፳፪ ። ዮሐ ፡ ፩ ፡ ፴፪—፴፬ ።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዮርዳኖስ ወንዝ እንዲጠመቅ ለምን ፈለገ ? ብሎ የሚጠይቅ ሰው ቢኖር እግዚአብሔር አምላክ ቀደም ሲል በነቢያቱ አድሮ ያናገረውን ትንቢት ይፈጽም ዘንድ ነው ። ባሕር አይታ



www.ethiopianorthodox.org

ሸሸች የርዳኖስም ወደ ኋላው ተመለሰ ። ተራሮችም እንደጊደር ዘለሉ ። በማለት ዳዊት በመዝሙሩ ተናግሮአልና ። መዝሙረ ዳዊት ፩፻፲፫ ፡ ፫—፯ ።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የጥምቀቱን ሥነ ሥርዓት እንደፈጸመ ወዲያውኑ ወደ ገዳም ገባ ። ነገር ግን ይህንየጌታን ጥምቀት ቤተ ክርስቲያን በየዓመቱ እያስታወሰች በደማቅ ሁኔታ ስታከብረው ትኖራለች ። በተለይም በኢትዮጵያ ሕዝበ ክርስቲያን የሚታየው የጥምቀት በዓል አከባበር እጅግ በጣም የሚያስደስትና ከፈጣሪም ክብርን የሚሰጥ ነው ። ወንዱ በሆታ ሴቱ በእልልታ ሲያከብሩ የሚታይባቸው የደስታ ስሜት ከቅን ልቡና ከንጹሕ ሕሊና እንደሚመነጭ ያስረዳል ። በእርግጥም እያንዳንዳችን በዛሬው ዕለት እጅግ ልንደሰትና ፈጣሪያችንንም በልዩ ልዩ ምስጋና ልናመሰግነው ይገባናል ።

ዛሬ ከሰይጣን ዳኛ ከኃጢአት ቀራኛ የተላቀቅንበት ከአምላካችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ዘንድ ይቅርታን ያገኘንበት ከእርሱም የተወለድንበት ቀን ነውና በእውነተኛ አምልኮት ልንደሰት ይገባናል ።

ገብረ ክርስቶስ ኃ/ማርያም

# ሥ ር ዓ ተ ጥ ም ቀ ት

ከቀሲስ ዳኛቸው ካሣሁን

በክርስቶስ ክርስቲያን ተብለው ያመኑ ምእመናንን ባመኑት እምነት ለማጽናትና በተቀደሰ ዓላማ ወደ ሕይወት መንገድ ለመምራት ከተወሰኑት ከሰባቱ የቤተ ክርስቲያን ሥርዓቶች አንዱ ሥርዓተ ጥምቀት ነው ።

ጥምቀት ማለት በቀድሞው ዘመን በዲያብሎስና በሰው መካከል በተፈጸመው የስሕተትና የተንኮል ውድድር ባልተገታ የሰው ምኞትና የሰይጣን ተንኮል ምክንያት ያጣነውን የሕይወት ቦታ ለማግኘት በኃጢአት የተጥለቀለቀውን ዓለም በእምነት ዋኝተን የምንሻ ገርበት መርከብ ነው ። ሰው ሁሉ በአብና በወልድ በመንፈስ ቅዱስም ስም ተጠምቆ ዳግመኛ በመወለድ የቤተ ክርስቲያን ወገን ለመሆን የሚችልበት ምሥጢር ይህ ምሥጢረ ጥምቀት ነው ። የአመነና በክርስቶስ ስም የተሠየመ ሁሉ ወደ ቅድስት ቤተ ክርስቲያንና ወደ እግዚአብሔር መንግሥት የሚገባበት ትክክለኛ በር ስለ ሆነ ከሌሎቹም ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን ሁሉ ከፍተኛውን ደረጃና ቅድሚያ የያዘ ነው።ምክንያቱም «ሰው ከውኃና ከመንፈስ ቅዱስ ዳግመኛ ካልተወለደ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም» ተብሎ ስለተጻፈ ነው ። ዮሐ ፡ ፫ ፡ ፭ ።

ጥምቀት በየዘመኑ ሲቀጥል በሚኖረው ሐረገ ትውልድ ሁሉ እየሠሩበት ለሰው ልጆች የሕይወት መክፈቻ ሆኖ ለዘለዓለም ጸንቶ የሚኖርና የማይለወጥ ስጦታ ነው ።

ከአዳም ባሕርይ የወረስነው የአሮጌ ሰውነት ጠባይ ቅንዓት ፡ ስህተት ፡ ዝሙት ስስት ፡ ትዕቢት ፡ ቂም በቀልና የመሳሰለው የርኩሰት ሥራ ሁሉ ተወግዶ በንጹሕ መንፈስ የእግዚአብሔር መንግሥት ወራሾች ለመሆን የምንበቃው ሊቀድስንና ሊያከብረን በሚችል በሚሥጢረ ጥምቀት ነው ። ጸንቶ የሚኖር ስጦታ ነው የተባለውም «እነሆ የሰማይና የምድር ሥልጣን ተሰጠኝ እንግዲህ ሒዱና አሕዛብን ሁሉ አስተምሩ በአብና በወልድ በመንፈስ ቅዱስም ስም አጥምቁ » ብሎ ጌታችን ክርስቶስ ከሙታን ተለይቶ ከተነሣ በኋላ ለሐዋርያት ያስተላለፈው አደራና ሥልጣን የማይሻርና የማለወጥ ስለሆነ ነው ። ማቴ ፡ ፳፰ ፡ ፲፰ ።



ስለ ጥምቀት ምሥጢር በነቢያት የተነገሩና በብሉይ ኪዳን የተጻፉ ምሳሌዎች አሉ ። በኖህ ዘመን የጥፋት ሰዎች ከጥፋት ውኃ መዳን ፡ ግዝረት ፡ የንእማን በዮርዳኖስ ተጠምቆ መዳን ፡ የዕብራውያን ባሕረ ኤርትራን መሻገርና የዮሐንስ የንስሐ ጥምቀት ናቸው ። ቆላ ። ፪ ፡ ፲፩ ። ዘኁ ፡ ፯ ፡ ፲፯ ።«ወንድሞቻችን ሆይ ይህንን ልታውቁ እወዳለሁ አባቶቻችንንሁሉ እንደጋረዳቸው ሁሉም በባሕር መካከል እንደተሻገሩ ሁሉንም ሙሴ በደመናና በባሕር አጠመቃቸው ። ፩ ቆሮ ፡ ፲—፲፪ ።

የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት በትርጓሜ እንደሚያስረዱት ሰይጣን የመጀመሪያዎቹን ሰዎች አሳስቶ ከእግዚአብሔር ሕግ ባስወጣቸው ጊዜ «አዳም የዲያብሎስ ባርያ ሔዋንም የዲያብሎስ አገልጋይ »ናቸው የሚል የበደል ማስታወቂያ ጽፎ አንዱን በሲኦል ሁለተኛውን በዮርዳኖስ አኑሮት ነበር ተብሎ ይነገራል ።

የሲኦልን በሞቱ የዮርዳኖስን በጥምቀቱ ለመደምሰስና የዲያብሎስን የበደል ደብዳቤ ከሰው ዘንድ ለማሻር ጌታ ኢየሱስ በፈለገ ዮርዳኖስ ከመጠመቁ አስቀድሞ ዮሐንስ መጥምቅ ለኃጢአት ሥርየት የንስሐ ጥምቀት ያጠምቅ ነበር ።

የዮሐንስ ጥምቀት ለዘመኑ ሕዝብ ለክርስቲያኖች ጥምቀት አርአያ ለመስጠትና የክርስቶስን ጥምቀት እንዲቀበሉ ለማዘጋጀት እንጂ ሁለተኛ መወለድን የሚያሰጥ ኃይል ያለው አልነበረም ። ሉቃ ፡ ፫ ፡ ፫ ።

ክርስቶስ የተጠመቀው በ፴ ዘመኑ ነው ። የመጠመቃችን መሠረትም እሱ ነው ። ሆኖም እግዚአብሔር ሰውን ከእናቱ ማሕፀን ሳለ ጀምሮ የሚባርክ ፡ የሚቀድስና የሚመርጥ ከመሆኑም በላይ ፡ ከፍ ያለ ጸጋን እንዲቀበሉ ሕፃናትን ወደ ዙፋኑ የሚያቀርብ ስለሆነ በጥምቀት የመንፈስ ቅዱስን ጸጋ እንድንቀበል በሕፃንነታችን ወራት መጠመቅ ይገባናል።በሕፃንነትና ካደጉ በኋላ በጉልምስና ጊዜ ስለመጠመቅ በክርስቲያን እምነት ተከታዮች መካከል አንዳንድ የሥርዓት መጋጨት አለ ።

ሆኖም እኔ ያልኩት እንጂ ሌላው የሚለው አይሁን ከሚለው የግትርነት ጠባይ በቀር ጥምቀት ከውኃና ከመንፈስ ቅዱስ ተወልዶ በዳግም ልደት ታድሶ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት መግባት ከሆነ በሕፃንነት ወይም በውርዝውና ጊዜ ቢደረግ የሚከለክል ሕግ አይደለም ።

ክርስቶስ በ፴ ዘመኑ ቢጠመቅም ልክ እንደዚሁ አድርጉ ብሎ የሰጠው ውሳኔ የለም ይልቁንም በሐዋርያት ዘመን ቤተ ሰቦች የሆኑት ሁሉ በሙሉ ይጠመቁ እንደ ነበር ተጠማቂዎቹ የክርስቲያን ልጆች ከሆኑ በሕፃንነታቸው ወራት ቢጠመቁ በትምህርታቸውና ባካሔዳቸው የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ ሊመራቸው ይችላል ። በክርስቶስ የክርስታያንን ስም ሳይቀበሉ በሌላ የእምነት ክልል የኖሩና ከጊዜ በኋላ ወደ ክርስቶስ ብርሃን ለመምጣት የተጠሩ ኮረዶችና ጎልማሶች ግን አስቀድመው የክርስቶስን ትምህርት የወንጌልን ቃልና የሃይማኖት መሠረት እንዲማሩና ዐውቀው እምነው እንዲቀበሉ ካመኑም በኋላ እንዲጠመቁ ማድረግ የሚገባ ነው ።

በሌላው ግን የኛይቱ ቤተ ክርስቲያን ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያንን ለምእመናን ጠንቅቃ ስታስተምር የክርስቲያን ወገን የሆኑት ሁሉ የጥምቀትን ጸጋ በሕፃንነት መቀበል የሚገባ መሆኑን ታውጃለች ። ጸንቶ የቆየው ሥርዓትም ይኸው ነው ። ስለ ምሥጢረ ጥምቀት በዚህ ብቻ ሳንወስን በብዙ ቦታና ጊዜ መነጋገርን ይጠይቃል ።

የጥምቀትን በዓል በየመቱ የምናከብረው ለምንድነው ? ጥምቀት በክርስቶስ በሞቱና በመቃብሩ ይመሰላል ክርስቶስ ለሰው ሁሉ ሕይወትን ለመስጠት እንደ ሞተ ከሙታንም ተለይቶ በሦስተኛው ቀን እንደ ተነሣ በስሙ ያመንንና የተጠመቅን እኛም እንደሱ በአዲስ ሕይወት እንነሣለን።



www.ethiopianorthodox.org

ስለዚህም የሕይወታችን መሠረትና መሪ ስለሆነ ከሰማያዊ ክብሩ ዝቅ ብሎ ሰውን ለማክበር በጸጋና በረድኤት ለማገናኘፍ በዮርዳኖስ ወንዝ ስለ ተጠመቀ በቸርነቱ የፈጸመውን ውለታ ለማሰብና ለማስታወስ እናከብረዋለን ።

ክርስቶስ ወደ ዓለም የመጣው እውነትን ትክክለኛነትንና ትሕትናን ለማስተማር ስለሆነ የጫማውን ክር እንኳን ሊፈታ በማይገባው በዮሐንስ እጅ ተጠመቀ ።

ዳሩ ግን በመለኮቱ ሰማይና ምድር ሊወስኑት የማይችሉ መጀመሪያና መጨረሻ የማይገኝለት አምላክ እሱ በተጠመቀ ጊዜ የዮርዳኖስ ወንዝ ውኃ ተጨነቀ ፤ ባሕር ሸሸ የዮርዳኖስም ወደ ኋላው ተመለሰ ። ተራሮች እንደጊደር ዘለሉ የመጣው ለድኅነት ለሕይወት ነውና ሁሉንም በትሕትና ፈጸመ ። የምወደው ልጄ ይህ ነውና እሱን ስሙት የሚለው ምስክርነትም በዚያች ዕለት በዮርዳኖስ ወንዝ ተመሰከረ ። እኛም ቃሉን በመስማት ትእዛዙን በመቀበል እንከተለዋለን በሱም የዘለዓለም ሕይወትን እንወርሳለን ።

# የመጀመሪያው ተአምር

ተአምር ማለት በእግዚአብሔር ሥልጣን የሚደረግ አንድ ዓይነት ኃይል ወይንም አስደናቂ ሥራ ነው ። —ለምሳሌ ድውያንን መፈወስ ፤ ዕውራንን ማብራት ፤ ሙታንን ማስነሣት ፤ አጋንንትን ማውጣት ይህን በመሳሰሉት ሁሉ የሚደረግ ነገር ተአምር ይባላል ።—

በመሠረቱ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሰማየ ሰማያት ወርዶ ከድንግል ማርያም ተወልዶ በ፴ ዘመኑ በዮሐንስ እጅ ከተጠመቀ በኋላ ዕለቱን ሳይውል ሳያድር ገዳመ ቆሮንቶስ ገብቶ ፵ መዓልት ፵ ሌሊት እንደ ጾመ ሁላችንም እናውቃለን — ፻ው ቀን ሲፈጸምም የሥራ ወይም የተአምራት መጀመሪያ ያደረገው የገሊላ አውራጃ በምትሆን በቃና ዘገሊላ ከሠርግ ቤት በመገኘት ውኃውን የወይን ጠጅ በማድረግ ነው —።

መጽሐፉ በሦስተኛው ቀን በቃና ዘገሊላ ሠርግ ሆነ ይላል — ይህም ማለት መዋዕለ ጾሙን ፈጽሞ ከወጣ በኋላ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የመጀመሪያውን ተአምር እንዳደረገ ያስረዳናል ።

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ሠርግ ቤት የተጠራበትንም ዕለት የካቲት ፳፫ ቀን እንደሆነ የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ይናገራሉ ። ነገር ግን በጥር ፲፪ ቀን የበዓሉ መታሰቢያ እንዲከበር የተደረገበት ምክንያት ከላይ እንደገለጽነው ሁሉ ክርስቶስ በዮሐንስ እጅ በዮርዳኖስ ወንዝ ስለ ተጠመቀና የተአምራቱም መጀመሪያ ውኃውን የወይን ጠጅ በማድረግ በመሆኑ ተአምራቱን ከጥምቀቱ በዓል ጋር ለማዛመድ ያህል ነው ።

የሆነ ሆኖ የሠርጉ ባለቤት ዶኪማስ የሚባል ታላቅ መንፈሳዊ ሰው ነበር ። ዶኪማስ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ከእናቱ ከቅድስት ድንግል ማርያምና ከደቀ መዛሙርቱ ጋር የደስታው ተካፋይ እንዲሆንለት በክብር ጠርቶታል ። ጌታም ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ወደ ሠርግ ቤት ሔደ ሰማያዊ ጌታ ወደ ምድራዊ ሰው ሠርግ ቤት መሄዱ እንደዕሩቅ ብእሲ ምድራዊ ደስታን በመሻት ሳይሆን የአምላክነቱን ኃይል ለመግለጽ መሆኑን ተአምራታዊ ሥራው ያስገነዝበናል ።

ወደ ሠርጉ ቤት የተጠራው ሕዝብ መብዛት ማነሱን ባናውቅም የሠርጉ ድግስ በመጠኑ ሳይሆን አልቀረም ። በዚህ ምክንያት የመጠጡ ድግስ ባለቀ ጊዜ ዶኪማስ ከፍ ያለ ድንጋጤና ኃፍረት ደርሶበት ከቤተሰቡ ጋር ሲነጋገር እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ሰማች፡፡ከዚያም ልጇዋ ኢየሱስ ክርስቶስ ተአምራት ማድረጉን ስለምታውቅ ልጄ ሆይ እነዚህ ሰዎች መጠጣቸው አልቆባቸዋል ስትል ነገረችው ። ጌታም የዚያን ሰው ችግርና ጭንቀት ተመልክቶ የእናቱ የድንግል ማርያምን ቃል ሰምቶ አማላጅነቷን በፍቅር ተቀበለ ።

ወዲያው እመቤታችን የሚላችሁን ሁሉ አድርጉ ብላ ሠራተኞችን አዘዘች ። እነርሱም በጌታ ትእዛዝ መሠረት ስድስቱን ጋኖች ውኃ እስከ አፋቸው ድረስ መሉዋቸው ። ከዚህ በኋላ በምርፋቁ አለቃ ማለት ለሠርጉ አስተዳዳሪ ቀድታችሁ ስጡት አላቸው የምርፋቁም አለቃ በተአምራት የተለወጠውን የወይን ጠጅ በቀመሰ ጊዜ ከጣዕሙ የተነሣ በጣም አደነቀ ። ሆኖም ውኃውን ከቀዱት ሠራተኞች በቀር ሊቀ ምርፋቁ ከወዴት እንደመጣ ስለአላወቀ ሙሽራውን ጠርቶ «ሰው ሁሉ አስቀድሞ መልካሙን የወይን ጠጅ ያቀርባል ከዚያም በኋላ መናኛውን አንተስ መልካሙን የወይን ጠጅ እስከ አሁን አቆይተሃል » ብሎ ታል የሐንስ ፡ ፪ ፡ ፩—፲፪ ።

በዚህም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የጋብቻን ቅድስናና አስፈላጊነት ሲያረጋግጥ ሲያጸና በቃና ዘገሊላ ሠርግ በተጠራ ጊዜ የመጀመሪያውን ተአምር በመግለጽ ጋብቻን ቀድሶታል ለማለት እንችላለን ።

የቃና ዘገሊላ በዓል የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ የመጀመሪያው ተአምር የተፈጸመበት ዕለት በመሆኑ ቤተ ክርስቲያናችን ከፍ ባለ ሥነ ሥርዓት ታከብረዋለች ። ይህ ታላቅ ተአምራታዊ በዓል በምእመናን ዘንድ ምን ጊዜም ቢሆን ድምቀት ያለውና ስሜትን የሚቀስቅስ ነው ከዚህ ላይ ሳናስታውሰው የማናልፈው ነገር አለ። ይኸውም የያዝነው ወራት ዘመነ መርዓዊ ተብሎ መጠራቱን ነው ።

ይህ ወራት ወላጆች የልጆቻቸውን ደስታ የሚያዩበት ወጣቱና ወጣቷ ጋብቻን የሚመሠርቱበት በቃል ኪዳን የሚተሣሠሩበት ሙሽራው ሙሽራዋን ሕይወቷን ሸየሚልበት ወራት ነው ። ይሁን እንጂ ምድራዊ ሕይወትን ብቻ ሳይሆን ሰማያዊ ሕይወትንም እንዲያገኙ የጋብቻው ሥነ ሥርዓት መፈጸም የሚገባው በቤተ ክርስቲያን ሕግና ሥርዓት በተክሊልና በሥጋ ወደሙ መሆን አለበት ። በሕጋዊ ጋብቻ ጸንቶ በመኖር ከእግዚአብሔር ዘንድ ዋጋ ያገኛል ። በወንዱና በሴቲቱ መካከል ያለውንም አንድነት ወይም ቃል ኪዳን ሊያጸናው የሚችለው ሥርዓተ ተክሊልና ቍርባን ነው

የቃናው ሙሽራ ጋብቻን በሚመሠርትበት ጊዜ ንጉሠ ሰማያት ወምድር ክርስቶስን በመጥራቱ በተደረገው ታምራት ከመደሰቱም ሌላ በቱ ተባርኮለታል ። ለሠርጉም የተጠሩት ሰዎች ሁሉ ክርስቶስ የባሕርይ አምላክ መሆኑን በዚህ አማኑኤልነት አይተው አምነዋል ።

ዛሬም ቢሆን እኛ ክርስቶስን በውነት ብንጠራው የቃናን ውኃ ወደ ወይን ጠጅ እንደለወጠው የእኛንም ሰውነት ከኃጢአት ወደ ጽድቅ ከኃሳር ወደ ክብር ይለውጠዋል ።

መ/ ኀይሌ ለገሠ



www.ethiopianorthodox.org

# ፓትርያርክ ፒሜን ኢትዮጵያን ጐበኙ

የሞስኮና የመላው ሩሲያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ ግርማዊ ንጉሥ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በአደረጉላቸው የክብር ጥሪ መሠረት ከጥር ፱ ቀን ፲፱፻፸፱ ዓ/ም ጀምሮ ኢትዮጵያን በኦፊሴል ይጐበኛሉ ።

ስለ ኢትዮጵያ ጉብኝታቸው ለአንድ የውጭ አገር የአብያተ ክርስቲያናት ግንኙነት ጋዜጠኛ ፓትርያርኩ በሰጡት መግለጫ መሠረት የኢትዮጵያ የሩሲያ አብያተ ክርስቲያናት ስለ አላቸው ግንኙነት በማስረዳት ሲገልጹ ከአለፉት ፪ መቶ ዓመታት ጀምሮ ግንኙነት አላቸው ብለዋል እ-ኤ-አ በ፲፰፻፹፰ ዓ/ም የመጀመሪያው የሃይማኖት ልዑካን በአርቶ ማንድራይት ፓይሲ ይመሩ የነበሩት ኢትዮጵያን ጐብኝተዋል ።

በእዚህ ዘመን ደግሞ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ልዑካን ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ሩሲያ የመጡት በእዚያን ጊዜ መስኮብ የክርስትና እምነት የተቀበለችበትን ፱መቶ ዓመታት ባከበረችበት መንፈሳዊ ሥነ ሥርዓት ላይ በመገኘት ነበር ።

በ፲፰፻፺፰ ዓ/ም በሐረሩ ሜትሮፖሊታን የሚመሩት የቤተ ክርስቲያን ልዑካን መንግሥቱን ወክለው ሩሲያን ጐብኝተዋል።

የሁለቱን ሀገሮች መንፈሳዊ ግንኙነት የዓለም ጦርነት ምክንያት ሆኖ ለጥቂት ጊዜ ያግደው እንጂ ኢየሩሳሌም በአሉት መልእክተኞች አማካይነት ግንኙነታቸው ሳይቋረጥ በአለፉት የሁለት ትውልድ ዘመናት ውስጥ በእዚህ ዓይነት ሲካሄድ ቆይቷል ።

አርቺ ማንድራይት ኒቆዲሞስ (አሁን የሌኒንግራድ ሜትሮፖሊቲን) እ-ኤ-አ በየካቲት ወር ፲፱፻፶፱ ዓ/ም ኢትዮጵያን ጐብኝተዋል በእዚያም የግርማዊነታቸው እንግዳ ሆነው በቆዩበት ጊዜ በልዩ ልዩ መንፈሳውያን ሥነ ሥርዓቶች ላይ በመገኘት ስለ ኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ለማወቅ ችለዋል ።

ግርማዊ ንጉሥ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሞስኮን በጐበኙበት ጊዜ የሞስኮና የመላው ሩሲያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ አሌክሲስ ስለ ግርማዊነታቸው ክብር ታላቅ ሪሴፒሲን በማድረግ ለግርማዊነታቸው ከፍተኛውን የቤተክርስቲያን ስጦታ የሆነውን የመጀመሪያው ደረጃ የልዑል ቭላድሚርን ኒሻን አበርክተዋል ግርማዊ ንጉሥ ነገሥትም ለፓትርያርክ አሌክስ የሥላሴን ኮርዶን ሊሻንና የወርቅ መስቀል ሸልመዋቸዋል ።

የታወቁ የኢትዮጵያ መንግሥት መልእክተኞች በየጊዜው በልዩ ልዩ ምክንያት በኦፊሴል ሞስኮን ጐብኝተዋል ።

እ-ኤ-አ በ፲፱፻፶፯ ዓ/ም በሊቀ ጳጳሳት አቡነ ዮሐንስ ገብረ ኢየሱስ የሚመሩ መንፈሳውያን ልዑካን መስኮብን ጐብኝተዋል።

ሊቀ ጳጳሳት አቡነ ቴዎፍሎስ (አሁን የኢትዮጵያ ፓትርያርክ) የሞስኩ ሚመተ ፓትርያርክነት እንደገና ተመልሶ የተቋቋመበት ፶ኛ ዓመት በዓል በ፲፱፻፷፪ ዓ/ም በተከበረበት ጊዜ የክብር እንግዳ ሆነው ተገኝተዋል ።

በ፲፱፻፷፱ ዓ/ም የጎጃም ሊቀ ጳጳስ አቡነ ማርቆስ ሞስኮ ላይ በተለይ ዘጎርስክ በተደረገው የጠቅላላ የሃይማኖት ተከታዮች የሰላም ኃይል ጉባዔ ላይ ተገኝተው ተካፋይ ሆነዋል ።

በ፲፱፻፷፩ ዓ/ም የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መልእክተኞች የሩሲያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ ፒሜን የመንበረ ፓትርያርክነት ሥልጣን ጠቅላላ ጉባዔ ባደረጉበት ጊዜ ተገኝተዋል ።

በሌላም በኩል ደግሞ የሞስኩ ፓትርያርኬት መልእክተኞች ብዙ ጊዜ ወደ ኢትዮጵያ እየተላኩ በልዩ ልዩ ጉዳዮች ጉብኝት አድርገዋል በ፲፱፻፷፯ ዓ/ም በሚኒስኩ ሊቀ ጳጳሳት ዕንጦንዮስ የሚመሩ በ፲፱፻፷፱ ዓ/ም ደግሞ በሌኒንግራድ ሜትሮፖሊታን ኒቆዲሞስ የተመሩ መንፈሳውያን ልዑካን ኢትዮጵያን ጐብኝተዋል ። ያን

በኋላም የግርማዊ ንጉሥ ነገሥት ቀ-ኃ-ሥ ፴፱ኛ ዓመት የዘውድ በዓል ንግሥ ሥነ ሥርዓት ላይ በመገኘት ከኢትዮጵያ አብያተ ክርስቲያናት መሪዎችና ከግርማዊነታቸው ቤተ ሰቦች ጋር ተወያይተዋል ።

የሩሲያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን መልእክተኞች እ-ኤ-አ በ፲፱፻፷፩ ዓ/ም ኢትዮጵያን ሁለት ጊዜ ጐብኝተዋል ፤ ይኸውም መጀመሪያ በጥር ወር የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማዕከላዊ ኮሚቴ አዲስ አበባ ላይ ስብሰባ በአደረገበት ጊዜ ፤ ሁለተኛም በግንቦት ወር የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ ሢመተ ጵጵስና ሥነ ሥርዓት ላይ ተገኝተዋል ።

የአሁኑ የፓትርያርክ ፒሜን ኢትዮጵያን መጐብኘት ደግሞ አንድ የሩሲያ ቤተ ክርስቲያን መሪ ኢትዮጵያን ሔዶ ሲጐበኝ በታሪክ የመጀመሪያ ምዕራፍ መሆኑ ነው ።

ፒሜን ለሩሲያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ፲፬ኛ ፓትርያርክ ናቸው የተወለዱ እ-ኤ-አዘ ሰኔ ፳፫ ቀን ፲፱፻፪ ዓ/ም በሞስኮ አቅራቢያ በምትገኘውኖግንስኪ ተብላ ከምትጠራ ሥፍራ ውስጥ ከአንድ ጸሐፊ ቤተ ሰብ ነው የተወለዱት የ፲፪ ዓመት ዕድሜ በሆናቸው ጊዜ ዘጎሮስክ ከሚገኘው ትሮይትስ ሴርጊዮ ላቭራ ተልከው ፒሜን የተባለውን ስመ ሥያሜ አገኙ ።

በ፲፱፻፶፩ ዓ/ም አርቺማንድራይት ፒሜን የእዚህ ገዳም የበላይ አስተዳዳሪ ሆነው ተሾሙ ከ፫ ዓመት በኋላ ደግሞ የሊቀ ጵጵስና ማዕረግ ተሰጣቸው ለብዙ ጊዜያት ጳጳስ ፤ ሊቀ ጳጳሳት ፤ ሜትሮፖሊታን በመሆን ለሞስኩ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን በልዩ ልዩ የመንፈሳዊ ግልጋሎት መልክ ላይ ድርሻቸውን አከናውነዋል ። በሞስኩ መንበረ ፓትርያርክም ውሥጥ ሊቀ መንበር በመሆን የአስተዳደሩን ክፍል ይዘው በመምራትና የቡንያሌንስኪ ገዳም (ከቴድራል) አስተዳዳሪ ሆነው አገልግለዋል ።

በሚያዝያ ወር ፲፱፻፷፪ ዓ/ም ፓትርያርክ አሌክሲስ ከእዚህ ዓለም በሞት ከተለዩ በኋላ በሩሲያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ሕግና ሥርዓት መሠረት ፒሜን የክሩቲትዚና የኮሎማ ሜትሮፖሊታን ሥልጣን ያዙ ።

የሩሲያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ጠቅላላ የፓትርያርክነት ምርጫ አድርጋ በድምጽ ብልጫ ሰኔ ፪ ቀን ፲፱፻፷፫ ዓ/ም ፒሜን የሞስኩና የጠቅላላው ሩሲያ ፓትርያርክ ሆነው ተመረጡ ።

ፓትርያርክ ፒሜን ለሞስኩና ለሌኒንግራድ መንፈሳውያን አካዳሚዎች የክብር አባል ናቸው ። ከፍተኛውን የሩሲያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ሽልማትና የሌሎችንም የኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ትርሲተ ክብር ተቀዳጅተዋል ።

ከ፲፱፻፷፪—፲፱፻፷፫ ዓ/ም ድረስ በአለው ጊዜ በእስክንድርያ ፤ በእየሩሳሌም ፤ በአንጾኪያ ፤ በሶርያና በሊማኖስ ፤ በኤላስ (ግሪክ) በሴርቢያን ፤ (ዩጎዝላቪያ) በቡልጋሪያ ፤ በሩሜንያ ፤ በፓሊሽ፤ በቼኮዝሎቫኪያ ፤ እና በጆርጅያን ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ተዘዋውረው ከመጐብኘታቸውም ሌላ በተመሳሳይ ጉብኝት የጠቅላላ አርመን ካቶሊኮች ፓትርያርኮችና ጄኔቭላይ የሚገኘውን የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ዋና መሥሪያ ቤት ጐብኝተዋል የ

በተጨማሪም ፓትርያርክ ፒሜን በመሬት ላይ በደረሰው የሰላም መቅሠፍት አስቸኳይ ፕሮብሌሞች ላይ በአሁኑ ጊዜ ስለሚያስፈልገው መፍትሔ ሲሉ ለሰላም ህልውና ከፍተኛ ትግልና ጥረት አድርገዋል



www.ethiopianorthodox.org

ከ፲፱፻፷፫ ዓ/ም ጀምሮ የዓለም አብያተ ክርስቲያናት የሰላም ኮሚቴ እና የሶቭዬት የውጭ ሀገሮች የባህል ግንኙነት ክፍል አባል ናቸው ።

ስለ ሰላም ይዞታ ሲባል በ፲፱፻፷፫ ዓ/ም ዋርሶ በ፲፱፻፷፯ ዓ/ም ጀኔቭላይ የዓለም አብያተ ክርስቲያናት የሰላም ጉባዔ ደርግ በተለይ ከዓለም በተውጣጡ ልዑካን ለሰላም ዋስትና ሲባል የጦር መሣሪያ ቅነሳ እንዲደረግ በ፲፱፻፷፱ ዓ/ም ሞስኮ በ፲፱፻፸፩ ዓ/ም ሔልሲንስኪ በተደረገው ስብሰባ ላይ ፣ የዓለም ሰላም ጉባዔ በ፲፱፻፸፱ ዓ/ም በርሊን ላይ በ፲፱፻፸፩ ዓ/ም በቡዳፔስት አድርጎት በነበረው ስብሰባ ላይ በመጨረሻም በ፲፱፻፸፫ ዓ/ ሞስኮ ላይ በጥቅምት ወር ተደርጎ በነበረው የሰላም ኃይል ስብሰባ ላይ ተገኝተዋል ።

በፓትርያርክ ፒሜን አሳሳቢነት የሩሲያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን፫ሚሊዮን ሩብልስ ስብሰባ በሶቭዬት የሰላም ልማት ሰጥታለች ።

የሰላም ኃይል ጉባዔ ተግባሩን በአከናወነበት ጊዜ ፓትርያርክ ፒሜን ለፈጸሙት ሥራ የውለታ መታሰቢያ ይሆናቸው ዘንድ የሰላም ክብረ ወሰን አቸናፊ ፣ (ፒስ ቻፒዮን) የተባለው የወርቅ ሜዳልና ፣ የሶቭዬት የሰላም ልማት ሜዳልን በስቶማው ተቀርጾ እንዲሸለሙ ተደርጓል ።

ፓትርያርክ ፒሜን ወደ ኢትዮጵያ ሲሔዱ የክብር ተከታዮች ሆነው አብረዋቸው የሚሔዱት ያቱላና የኤሌቭ ሚትሮፓሊታን እና የሞስኮ ፓትርያርኩች የውጭ ቤተ ክርስቲያን ግንኙነት ክፍል ሊቀ መንበር ፣ የ ሊዮ የሩሲያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ሲኖዶስ ነዋሪ አባል እና የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማዕከላዊ ኮሚቴ አባል ፣ የ ሎኮላምልክ ሊቀ ጳጳስ የሞስኮ ፓትርያርኬት የጋዜጣና የመጽሔት የሕትመት ክፍል ኃላፊ ብላድሜር ፣ የዲሞትሮቭ ሊቀ ጳጳስ የሞስኮ መንፈሳዊ አካዳሚና ሴሚናሪ ኃላፊ ፣ ጳጳስ ክሪዘሶት የሞስኮ ፓትርያርኬት የውጭ ሀገር ቤተ ክርስቲያን ግንኙነት ም/ሊቀ መንበር የሪያዛን ጳጳስ ስምዖንና የሌሎችም መንፈሳውያን ግልጋሎት ኃላፊ የክብር ተከታዮች ሆነው ወደ ኢትዮጵያ ይመጣሉ ።

# የኢትዮጵያና የሩሲያ መንፈሳዊ ግንኙነት

በፍልስጥኤም ባለው የኢትዮጵያ የመንፈሳዊ ሥፍራ ኢትዮጵያውያን ከሩሲያውያን ምእመናን ጋር ከ፲፭ኛው እስከ ፲፯ኛው ምዕት ዓመታት ውስጥ ተዋውቀዋል ይህንን የኢትዮጵያና የሩሲያን ጥንታዊ የሆነ መንፈሳዊ ግንኙነት ለማስረዳት ሲባልና ከኢትዮጵያውያን ክርስቲያኖች ጋር ለመተዋወቅ አርቸማንዳሪቲ አግሬኒ ኢየሩሳሌምን እንደ ኢሮፕ ዘመን አቆጣጠር ፩ሺ፫፻፸ ዓ/ም ገደማ ማለት የዛሬ ፮፻ ዓመት መጡ እኒህ መነኩሴ ከስምሌንክስ ተነሥተው ነበር ወደ ኢየሩሳሌም የመጡት ጽሑፍ እንደሚናገረው እኒህ ሰው ነበሩ ለመጀመሪያ ጊዜ የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ መቃብር በሚገኝበት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በብዛት ከኢትዮጵያ መነኮሳት ጋር ሆነው በሥርዓተ ቅዳሴው አፈጻጸም ላይ ከኢትዮጵያውያን መነኮሳት ጋር ያገለገሉት እንደ ኢሮፕ ዘመን አቆጣጠር በ፩ሺ፷፻፹ ዓ/ም የእግሬን ሀገር ሰው የሶሞሌንስኩ ነጋዴ ሲሲ ፖንዝያኮቭ ከሞስኩ የንግድ ሸቀጣ ሸቀጦችን ይዞ ኢየሩሳሌም ገባ የፓዝኒያኮቭ መጽሐፍ ስለገዛው እንደሚያስረዳው በግብጽና በፍልስጥኤም ጉብኝቱ በጻፈው ውስጥ የኢትዮጵያ ምእመናን በፍልስጥኤም በሚል መነሻ በጣም ጠቃሚ የሆኑታሪኮችንጽፏል በእዚያው ላይ ሲገልጽ የኢትዮጵያ መንፈሳዊ ጸሎት ሕሊናውን እጅግ አድርጎ የማረከው የትኛው እንደሆነ ሲያመለክት እንዲህ ብሏልየኢትዮጵያውያን መንፈሳዊ ሥነሥርዓት በኢየሩሳሌም በሚፈጸምበት ጊዜ ደስ የሚያሰኘው የስብሐተ እግዚአብሔር ዜማ ፣ አቋቋሙ ፣ ወረብና ውዝዋዜው የኢየሩሳሌምን መንፈሳዊ ቤተ ክርስቲያን እጅግ አድርጎ በመንፈስ ይመራዋል ዜማቸው በሰብአዊ አካል ውስጥ የሚተላለፍ ድምፅ ሳይሆን የመላእክትን ምሥጋና የመሰለ ነው ብሏል ።

በ፲፯ኛው መቶኛ ክፍለ ዘመን ላይ በሞስኮ ውስጥ ስለኢትዮጵያከተጻፉት ሌሎች ዜናዎችይልቅ የበለጠ መረጃና የኢትዮጵያ ታሪክ በመባል ተዘጋጅቶ የቀረበው ታሪክ ኢትዮጵያውያንን ሞስኮባውያን የበለጠ ሊያውቁ ችለዋል ።

እንደ ኤውሮፕ ዘመን አቆጣጠር በ፲፮፻፹፩ ዓ/ም የጀርመኑ ተወላጅ የቡስ ሉዮልፋስ በመስኮብ ሀገር ተገኝቶ ስለኢትዮጵያ ታሪክ መሠረተ ጥናት እንዲገኝ ያደረገውን ዝነኛ መጽሐፉን ሂስትሪ ኦፍ አቢሲኒያ ማለት የሐበሾች ታሪክ የተባለውን መጽሐፉን አሳተመ ። የመጽሐፉንም ቅጅ በዚያን ጊዜ የንጉሣዊ ቤተሰብ ወንድማማቾች ለነበሩት የሐንስና ጴጥሮስ በኋላም ቄሣር ቀዳማዊ ጴጥሮስ ተብለው ለተሰየሙት ላኩላቸው መጽሐፉ ለልዑላኑ የደረሰው እንደኤሮፕ ዘመን አቆጣጠር መጋቢት ፲፩ ቀን ፲፮፻፹፫ ዓ/ም ነበር ከዚያ በኋላ በ፲፮፻ ፹፬ ዓ/ም ላይ መጽሐፉ በእትም ተባዝቶ ለቄሣሮችና ለባለ ሥልጣናቶቻቸው ጭምር እንዲዳረስ ተደረገ ከ፫ ዓመት በኋላ ደግሞ የጀርመን ተማሪዎች የኢትዮጵያን ፣ ታሪክ በዚያ ለማሳወቅ የመጀመሪያዎቹ ስለነበሩ ኢትዮጵያ በተወሳች ቁጥር የልብ ኩራት ይሰማቸው ነበር ።

የኢትዮጵያ ታሪካዊ ዜና እጅግአድርጎ ያስደሰተውና ሕሊናውን ፣ የመሰጠው የስዊድን ምሑር የሆነ እስፓር ቤን ቤልድ ለሩሲያን ቄሣር መደሰቱን ገልጾ ጽፎለታል ፊቃዱንም በመጠየቅ ይኸው የኢትዮጵያን ታሪክ የሚገልጸው መጽሐፍ አንድ ልዩ የተርጓሚ ጓድ ተቋቁሞለት በሙስኮብኛ ቋንቋ እንዲተረጎም ባቀረበው ጥያቄ መሠረት ኒኮላስ እስፓፋሪዮስ በተባለግሪካዊው የበላይ ጠባቂነት እንዲተረጎም ተደረገ ኒኮላስ በመስኮብ ሀገር ታላቅ ሰው ከመሆኑ የተነሣ በቻይና የሩሲያ አምባሳደርም ሆኖ ሠርቷል ።

የኢትዮጵያን ታሪክ ወደ መስኮብኛ ለመተርጎም ተወክለው የነበሩት ከፖላንድ ባየሎብትስኪ ከጀርመን ጉብኖር ሲሆኑ ከቤሎሩ ሲያን፣ ደግሞ እስታች ሆድ ዛሎውሶኪ ነበሩ ። ከዚህም የተነሣ ለመጀመሪያ ጊዜ የኢትዮጵያን ታሪክ አቀላጥፎ በማጥናት ዲዊሩሲያን ቀዳሚ ሆነዋል ጀርመናዊው ሎዶልፋስ የሐበሻ ታሪክ የሚለውን መጽሐፉን ከላቲንኛ ወደ ሩሲያ እ ኤ ዘ አ በ፲፮፻፺፩ ዓ/ ም መተርጎሙን አመልክቷል ። የዚሁ ጽሑፍ ቅጅ የሆኑ የእጅ ጽሑፎች በሌኒንግራድ ውስጥ እንዲቀመጡ ተደረገ ይሁን እንጂ በ፲፯ኛው ክፍለዘመን ላይም ሆነ ወይንም ከዚያ ወዲህ በእጅ የተጻፉት መጻሕፍት በማኅተም ስላልተባዙ በብዙ ሰዎች ዘንድ ሳይታወቁ ቀርተዋል ።

ሊዮልፋስ የጻፈው መጽሐፍ አሁንም ቢሆን በሞስኮ የሩሲያና የኢትዮጵያ ጎብረት በሚለው ክፍል ውስጥ በክብር ተጠብቆ የሚገኘው ።

አፈወርቅ አስግደ





www.ethiopianorthodox.org

# “ለጥምቀት ያልሆነ ቀሚስ”

ለጥምቀት ያልሆነ ቀሚስ ይበጣጠስ ማለት የበዓሉን ታላቅነት የሚያበስር የአባቶች ምሳሌያዊ አነጋገር ነው ።

(በሀገራችን) በኢትዮጵያ የሚከበሩ መንፈሳውያን በዓላት አሉ ። ከነዚህም መካከል የጥምቀት በዓል አንዱ ነው ። የጥምቀት በዓል በአከባበሩ ከሌሎቹ የተለየ ድምቀትና መወደድ አለው ። የሚከበረውም በአደባባይ ምቹ የሆነና ውሀ ያለበት ቦታ ተመርጦ ድንኳን ተተክሎ ዳስ ተጥሎ ነው ። ሊቃውንት ስለበዓሉ አከባበር (ከምን እንደ ተወረሰ (እንደተገኘ) ሲያስረዱ አብርሃም ጊራራ በሚባለው ቦታ እንግዳ ሆኖ ተቀምጦ ሳለ ከመከራ ላዳነውና ተሰዶ በሔደበት አገር ላስደሰተው ለእግዚአብሔር መሥዋዕያን ሠራ ሰባት ቀን የደስታ በዓል አደረገ አብርሃም በዚያን ጊዜ ለእርሱ ለአሽከሮቹና ለቤተ ሰቦቹ ድንኳን አስተክሎ በዳስ በጥላ ሆኖ በዓሉን አክብሮ ነበርና ይህን የመሰለ ሥርዓታዊ ዝግጅት ከእሱ ቀጥሎ በሙሴ ሲደረግ ይኖር ነበር ከዚያ ተያይዞ መጥቶ ድንኳን ተክሎ ዳስ ጥሎ በዓል ማክበር በኢትዮጵያ የተለመደ ሆኗል በማለት ያስረዳሉ ። በሌላ በኩል ደግሞ ጥምቀት በበዓለ መጸለት ምትክ የገባ ስለ ሆነ አይሁድ በዓለ መጸለትን ከቤታቸው ወጥተው ድንኳን ተክለው ዳስ ጥለው ያከበሩት ስለነበር በዚያ ባህልና ልማድ ነው የሚሉም አሉ።

በየዓመቱ ጥር ፲ ቀን የከተራ ዕለት ማለት የጥምቀት ዋዜማ (ጥምቀት እንደነገ ሆኖ ዛሬ) የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ወደወንዝ ታቦት እየወረደች የእግዚአብሔር ቃል በውሆች ላይ ተገለጠ የምስጋና አምላክ ድምጡን ሰጠ እግዚአብሔር በውሆች ላይ ታየ ያለውን ቃል መሠረት በማድረግና ጌታ እግዚአብሔር ተገልጧልና በደስታ በዓል አድርጉ የሚለው ቃል ትንቢት ይፈጸም ዘንድ መታሰቢያውን ታከብራለች መዝ ፳፱ ፫ ፻፲፰ ፳፯ ማ፥ ፫ ፲፫-፲፯ ።

በዚሁ ዕለት ምእመናንም የየአጥቢያቸውን ታቦት አጅበው በየቦታው ያደርሳሉ በበነጋታው ጧት ማየ ምንዛሁን ለመረጨት ይመጣሉ በዚህም ለጥምቀት ያልሆነ ቀሚስ ይበጣጠስ እንደሚባለው ያለው አዲስ ገዝቶ ለብሶ የሌለው ተውሶ ይህም ያልሆነለት ያለችውን አጥቦ ሁሉም አፍአዊ ሰውነታቸውን በአዲስ ልብስ አሸብርቀው ነው ። የማየ ምንዛሁም ሥነ ሥርዓት ከተፈጸመ በኋላ ወንዱ በሆታ ሴቱ በእልልታ የየአጥቢያቸውን ታቦት አጅበው በየቦታቸው ያስገባሉ እንዲሁም በየአደባባዩ በመዘፈን የደስታ በዓል ያደርጋሉ ። የጥምቀት በዓል በየዓመቱ በዚህ ዓይነት ሁኔታ ሲከበር እናያለን ምንም እንኳ በአዲስ ልብስ አሸብርቆ መታዬቱ የኢትዮጵያ ክርስቲያኖች ለበዓለ ጥምቀት የሚሰጡትን ከፍተኛ ክብር ቢያስረዳም ይህ ብቻ የበዓሉን ምሥጢር አይገልጽም ።

በየዓመቱ ይህ በዓል በደረሰ ቁጥር በኅብረተ ሰቡ ዘንድ ልዩ ልዩ እንቅስቃሴና ዝግጅት ይደረጋል ምንም ችግረኛ ቢሆን ለጥምቀት አዲስ



ልብስ ለመልበስ ጥረት የማያደርግ የለም አንዳንዶቹ ደግሞ መስለው ለመታየት ብድር ይገቡና ዕዳ ከፋዮች ይሆናሉ ፤ትንኝና ዝሆን ውሀ ለመጠጣት አብረው ወደወንዝ ቢወርዱም የሚጠጡት እንደየአቅማቸው ነው እንደዚሁም ሁሉ ማናቸውም ሰው የሚያደርገው ሁሉ እንደየዓቅሙ መሆን አለበት ይህ ሁሉ ጥረትና ድካም የሚደረገው አምሮ ሠምሮ አጊጦ ለመታየት ነው ይህ በሰው ዘንድ እንጅ በእግዚአብሔር ዘንድ ቦታ የለውም ይህ ታላቅ መንፈሳዊ በዓል የልብስ ዓይነት ብቻ መታያ መሆን የለበትም«ለጥምቀት ያልሆነ ቀሚስ ይበጣጠስ»የሚባለውም በእግዚአብሔር ፊት ንጹሕ ሆኖ ለመታየት የሚያስችል እንጅ ለምንዝርና ለመሳሰለው እስከፊ ተግባር መሆን የለበትም (አለመሆኑን ማስታወስ ያስፈልጋል ። ሰው ፊትን ያያል እግዚአብሔር ግን ልብን ያያል እንደተባለው በእግዚአብሔር ፊት ንጹሕ አድርጎን ማቅረብ የሚገባን የልብሳችንን ጽዳት ብቻ ሳይሆን የልባችንን ንጽሕና መሆን አለበት እስቲ እራሳችን እንመርምር በአዲስ ልብስ የተሸፈነው አካላችን ንጹሕ ነወይ በኃጢአት አላደፈምወይ ? ኃጢአታችንን ተናዘን በንስሐ ካልታጠብን አዲስ መልበሳችን ብቻ እግዚአብሔርን አያስደስተውም እግዚአብሔር ከኃጢአት ታጥበን የምንነጻበትን ንስሐን ሠርቶልናል ታዲያ ለምን ታጥበን አንነጻም ።

በወንጌል ትምህርት የመጀመሪያውን ምዕራፍ ይዞ የሚገኘው ንስሐ ነው ስለንስሐ በቅዱሳት መጻሕፍት ያሉትን እንመልከት በዚያም ወራት መጥምቁ ዮሐንስ በይሁዳ ምድረ በዳ እየሰበከ መጣ እንዲህ እያለ መንግሥተ ሰማያት ቀርባለችና ንስሐ ግቡ እያለ ማቴዎስ ፫ ፩ ይህ ቃል የተነገረው በዘመነ ብሉይ መጨረሻና በዘመነ ሐዲስ መጀመሪያ ነበር ኋላም ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌልን ለማስተማር በጀመረበት ጊዜ ለትምህርት መግቢያ ያደረገው ይህንኑ ቃል በማጽናናት ነው በተጨማሪም ኃጥአንን ወደንስሐ ለመጥራት እንጅ ጻድቃንን ለመጥራት አልመጣሁም ንስሐ ከማይሹ ከዘጠና ዘጠኙ ጻድቃን ይልቅ ንስሐ ስለሚገባ አንድ ኃጢአተኛ በሰማይ ደስታ ይሆናል በማለት አስተምሯል ማቴዎስ ፱ ፲፫ ሉቃስ ፲፭ ፯። በዘመነ ብሉይ ታጠቡ ሰውነታችሁንም አንጹ የሥራችሁን ክፋት ከአይኔ ፊት አስወግዱ ክፉ ማድረግን ተዉ መልካም መሥራት ን ተማሩ ፍርድን ፈልጉ የተገፋውን አድኑ ለደሀ አደጉ ፍረዱለት ስለመበለቲቱም ተምዋገቱ ኃጢአታችሁን እንደአለላ ብትሆን እንደ አመዳይ ትነጻለች እንደደምም ብትሆን እንደባዘቶ ትጠራለች ይላል የእግዚአብሔር ቃል የወደቁ አይነሡምን የሳቱስ አይመለሱምን እንግዲህ የኢየሩሳሌም ሰው ስለምን ወደኋላው ይመለሳል ተንኮልን ይዞአል ሊመለስም እምቢ ብሎአል ሰማሁም ቅን ነገር አልተናገሩም ማናቸውም ምን አድርጌአለሁ ብሎ ከክፋቱ አልተመለሰም ንስሐ የገባ የለም ። ንስሐ ግቡ ኃጢአትም ዕንቅፋት እንዳይሆንባችሁ ከኃጢአታችሁ ሁሉ ተመለሱ የበደላችሁትን በደል ሁሉ ከእናንተ ጣሉ አዲስ ልቡና አዲስ መንፈስንም ለእናንተ አድርጉ በማለት በነቢያት አድሮ



www.ethiopianorthodox.org

የተናገረ ዋህድ ቃለ እግዚአብሔር ዛሬ በአጭር ቁመት በጠባብ ደረት ተወስኖ ሥጋ ለብሶ መንግሥት ሰማያት ቀርባለችና ንስሐ ግቡ እያለ ይጠይቀናል።እነሆ ከደጃፍ ቆሜ ደጅ እመታለሁ ቃሌን ሰምቶ የከፈተልኝ ቢኖር ያን ጊዜ ገብቼ ከሱ ጋር እርፋለሁ እርሱም ከኔ ጋር ይኖራል ይላል (የእግዚአብሔር ቃል) ራዕይ ፫ ፳ ኢሳይያስ ፲፰-፲፱ ፰ ፯ ።

ወዳጆች ይህን ጥሪ እንቀበል ሁላችንም ራሳችንን እንመርምር በንስሐ እንታጠብ በአዲስ ልብስ ለማጌጥ የምንፈልግ ለምን በሐዲስ ልብ አናጌጥም በውጭ ማማር ብቻ አይበቃም ልብሳችን አካላችንን እንጂ ኃጢአታችንን አይደብቅም ቅዱስ መጽሐፍ ለናንተ አፍአዊ ጌጥ አይሁን ይላል የልቡናችሁን አሳብ አድሱ እግዚአብሔር በሃይማኖት በቅንነት በንጽሕና ያደሰውን ሰውነት ልበሱ ኤፌ ፬ ፪ ፳፬ ሰው በኃጢአት የተበላሸውን ሰውነት በንስሐ አድሶ አዲስ ሰውነት ለብሶ ካልተገኘ አዲስ ልብስ መልበስ ብቻ በቂ አይሆንም ቅ/ ጳውሎስ አሮጌውን ሰውነት ከነ ሥራው ጣሉ (ተውት) ፈጣሪን የሚመስለውን በአእምሮ የጸናውን አዲሱን ሰውነት ልበሱ ይላል አዎ አዲስ ልብስ ከመመኘት አዲስ ሰውነት መመኘት ያሻል ለአዲስ ልብስ አዲስ ሰውነት ያሻል (ያስፈልጋል) ሁላችንም ለአዲስ ሕይወት ለአዲስ ሥራ በሃይማኖት እንዘጋጅ።

ከጌታቸው አበራ ።



# EPIPHANY (TIMKET)

ABRIEF GENERAL KNOWLEDGE ABOUT THE HISTORICAL BACK GROUND.

We have learned from the Holy Scripture that no one ever saw God. We may ask then how do we know about Him? We know about God because He reveal Himself to us. But how does God do this? He does this mainly in three ways through the world He created and which we can see through his prophets.

And through His only Begotten son Jesus Christ, who revealed to us every thing that we need to know about, God the father, God the son, and God the Holy Spirit.

We can not know about God ourselves. Therefore, God through his prophets and through our Saviour reveals to us all that we need to know for our salvation.

The Books of the Old Testament, on the one hand tells us how God created the world, how people sinned, how God drove them out of Eden and how God prepared the people for the coming on the earth of the Son of God. The Old Testament therefore, is the old covenant or agreement of God with man and His promise to man of a Divine Saviour and the preparation of men to receive Him.

The Books of the New Testament, on the other hand bring us the good news, about the Birth, Epiphany, Earthly life, teachings, death, Resurrection and Ascension into Heaven of our Lord Jesus Christ.

Originally God made a happy and beautiful world and He made man a master of this world. He created man in His own image, and male and female he created? them and God blessed them1:27).

God wanted man to serve and obey him, because of love, not-just because of being told to, but the Bible tells us a story wich shows how man lost this life of happy obedience and love.

Adam and Eve were commended by God not to eat the fruit of the forbiden tree, which was in the middle of the garden, because they might die if they did. But they ate, because the spirit of evil crept into the garden and told them that they will not die. So when Adam and Eve choose to disobey God, they obeyed the spirit of evil, they allowed him to inter to their life, to become their master. This then was the end of their happy life in the Garden of Paradise.

Many thousands of years had passed since Adam and Eve had disobeyed God and has been driven out of the Garden of Paradise. But the people rememberred that God had promised and fortold that He would one day send a redeemer to save mankind. They remembered also that God has told Abraham that in him all nations would be blessed, while Jacob had fortold that from the tribe of Juda and the descendants of David would come the Sviour of the world.



www.ethiopianorthodox.org

Most of the Nations of the world had turned away from the true God and worshiped gods that were false. But God watched over the Israelites and sent them many prophets so that they would not forget Him. (The true God.) The prophets taught the Israelites people to fulfil the commandments of the law. They fortold that the time was nearing when the Messiah or the promised Saviour, would appear on the earth.

Not all Israelites understood the words of the prophets in the right sense, most thought the Messiah would appear as a powerful earthly King who would free the Israelites from the yoke of the Romans. But there were also people who did not expect a powerful earthly King who would rule over Israelites Kingdom, But one who would free mankind from the chains of sin and return them to good, following the advice of the prophets, they tried to live in a good life according to the law of Moses. They prepared themselves to meet their Saviour by avoiding all kinds of evil things. There were not many such people. In fact this good people went almost unnoticed in the everyday life of those times. But God saw their righteousness and through them, He fulfiled, His promised to send the Missiah.

Thuse, in order to fulfill what have been fortold by the prophets, the Saviour of the world was born from the Virgin Mary, who was the daughter of Joachim and Anna, whom they were the descendants of King David.

We remember then, how Adam and Eve did not accept God's will, and disobeyed.

But the Virgin Mary, accepted and obeyed, and Jesus Christ was born to her, Jesus Christ who is the Saviour of all of us. Many awaited as a powerful King,was born in the most humble of surrounding in a manger. The first to see him and worship him were the Angels and the shepherds, after them came the rich wise men, who learned from the star that the King not only of the Jews but of all the world, had been born, and they came from far of land to worship Him and offer Him their gifts. The Holy Gospels tell us how the Angels and the people gloried Chrsit and how the stars served Him; as a whole Heaven and Earth join to gloryfy Him.

We have also read that when John the forerunner was born, Zachary, his father repeated the words that the Angle said about this Son, "He shall be a great prophet of God and shall show people the way to salvation through repentance. He shall be the forerunner of the saviour and shall prepare the way for Him."

Thus when John was still very young he went to the wilderness. There he lived-all alone. And what mattered much more to John than clothes and food was that he could pray undisturbed, to God, and listen to God's voice. So he spent all his time praying and doing penance. In this way he prepared himself for the work which God called upon him to do.



Then one day, when John was grown up, he knew that the time had come for him to begin his work. He left the wildernes and went along the river Jordan speaking God's message to the people who lived there, He would say to them, "*repent*, for the kingdom of Heaven is at hand." He told all of them how they must prepare for the coming of Jesus Christ, the Messiah who was promised for many years.

revealed, "He is my Beloved Son with whom I am well pleased."

On this Holyday among the popular cermonies that are performed is the blessing of water. We do this because we want to remember the way in which God blessed the water, of the river Jordan, when Christ Our Lord was baptized in it.

Thence, we have always to keep in mind that Timket is a religous and spiritaul festival and social fes-



*The Nativity*

The Baptism of Christ is as important as His nativity as far as His appearance among men, as the Son of God is concerned. As Christ's Birth is a starting point of His Human Life so also His baptism is the starting point of this Public life and ministry. Besides it was at his baptism that the Divine voice

tivities connected with it are incidential. The appearance of God among men, always remembering that it is the appearing of God on earth which has brought to this world that wonderful spirit with which almost every body feels himself filled. Besides, Christ by His baptism teaches us that every



www.ethiopianorthodox.org

one should be baptized. tThe very first mystery or sacramen in which our church takes part in that of *baptism*.

However, the briefest and may be the most complete message of Epiphany (Timket) would be this. The son of God has appeared on earth, becoming a son would be this. The son of God has appeared on Earth, becoming a Son of man in order that sons of men may some day appear in Heaven as sons of God.

May the Lord make us worthy of this glorious destiny.

AMEN



## *THE LEITURGICAL SERVICE ON OCCASION OF EPIPHAYN FEB. 19, 1974 MORNING WOIKSHIP*

KYRIGIMA (MISBAK)

The sea looked and fled,
Jordan turned back,
The mountains Skepped like rams The hills like lambs.
PSAL, 114.3 - 4

Then Jesus came from Galilee to the Jordan to John,

**Reading to be said by a deacon during the blessing of the water.**

But when the goodness and laving kindness of God our savior appeared. Tit 3. 4 — 8

1st Joh. 5. 5. Who is that overcomes the world

Acts chapt 10 v 34 and Peter opened his mouth.

1 **KYRIGMA** WHEN THE WATERS SAW THEE, O GOD
WHEN THE WATERS SAW THEE,
THEY WERE AFRAID PSA. 77 16.

Luk, 21 . 21 Now when all the people were baptized till the end.

**Kyrigma** to be said by deacons during the blessing of the water

**1st Kyrigma** The voice of the Lord is upon the waters:
The God of Glory thunders
The Lord, upon many waters. PSA, 29. 3 :

**Reading** MATT. **3 1** till the end.

2nd **Kyrigma** (MISBAK) WHEN THEWATER SAW

**Reading** MARK. **ch .** 3. **1 - 12** THE BEGINING OF THE GOSPELS OF JESUS CHRIST

3rd **Kyrigama** THE SEA LOOKED AND FLEED

**Reading** LUK **. 3 . 1 - 23.** IN THE FIFTEENIH YEAR OF THE REIGN OF TIBERIUS CAESAR,

**4th Reading by a Decon.** GALAT. Chap. 3 - 18 - 29

1St Joh. ch. 5 5 - 11.

Acts ch 13 16 - 27


**Kyrigma** (MISBAK)

What ails you. O sea that you flee? O mountains, that you skip like rams?
O hills, like lambs. Psal 114. 5.

**Reading Joh** 1. 7 - 17



www.ethiopianorthodox.org



*His Holiness Pimen Patriarch of Moscow*

# The First Visit of Patriarch Pimen

Pimen, Patriarch of Moscow and All Russia, head of the Russian Orthodox Church, arrived in Ethiopia on January 17on an official visit at the invitation of Haile Selassie I Emperor of Ethiopia.

A staff member of the Church Relations Department of the Moscow Patriarchate said, that contacts between the Russian Orthodox and Ethiopian Churches began in the second half of the past century, and in 1888 the first Russian religious mission headed by Archimanrite Paisi visited Ethiopia. In the same year representatives of the Ethiopian Church arrived in Russia for the first time to attend the celebrations on the occasionof the 900th anniversary of the adoption of christianity in Rus. In 1895 Church leaders headed by Metropolitan of Harrar were members of a government delegation of Ethiopia which visited Russia.

World wars interrupted these contacts which were revived only in 1948 through religious missions in Jerusalem and become especially active in the latest two decades. Archimandrite Nikodim (now Metropolitan of Leningrad), visited Ethiopia in February 1959. He made a detailed acquaintance with the life and activities of the Ethiopian Church and was received by Emperor Haile Selassie I.

During the visit of the Ethiopian Emperor to the USSR in the summer of the same year, Alexis, Patriarch of Moscow and All Russia, gave a reception in honour of the distinguished guest at Which he presented Haile Selassie I the highest Church award— the Order of Prince Vladimir, First Class. The Emperor awarded the Order of the Holy Trinity and a gold cross to Patriarch Alexis.

Official delegations of religious leaders of Ethiopia have of late visited the Soviet Union on many occasions. In 1966 a delegation of clergymen led by Archbishop Yohanns Gebre Eyesus of Tigre,visited the USSR. Archbishop Abuna Theophlos (now the Patriarch of the Ethiopian Church), was an honorary guest at the celebrations in 1968 on the occasion of the 50th anniversary of the restoration of the patriarchate in the Russian Orthodox Church in Moscow. In 1969 Abuna Markos, the Archbishop of Godjam,rattended the Zagorsk Conference of the follo-wars of all religions in the USSR in defence of peace. In 1971 representatives of the Ethiopian Church were present at the General Council of the Russian Orthodox Church and at the enthronement of Patriarch Pimen.

On the other hand, several delgeations of the Moscow Patriarchate visited Ethiopia in 1966 a delegation led by Archbishop Anthony of Minsk and in 1969 a delegation led by Nikodim, Metropolitan of Leningrad. The arrival of the latter coincided with the 39th anniversary



www.ethiopianorthodox.org

of the coronation of Emperor Haile Selassie I The members of the delega -tion attended all the undertakings which were held in connection with this date, and met with top state and Church leders and members of the Emperor's family.

Delegations of the Russian Orthodox Church visited Ethiopia twice in 1971 in January during the meeting of the Central Committee of the World Council of Churches and in May at the enthrone -ment of the Patriarch of the Ethiopian Church.

This is the first time in the history of relations between the countries that the head of the Russian Orthodox Church is going to visit Ethiopia. Pimen is the 14th Patriarch of the Russian Prthodox Church. He was born on June 23, 1910 in Thecity of NogoinskMoscowRegion, in the family of an office worker. At the age of 17 he was ordained at the Troitse - Sergiyeva Lavra (Zagorsk) and given the name of Pimen. In 1954 Archimandrite Pimen was appointed superior of this monastery and three years later was ordainded Bishop. For a number of years Bishop, Archbishop, Metropolitan Pimen ruled many dioceses of the Russian Orthodox Church and the affairs of the Moscow Patriarchate, Chairman of the Business Management and the Superior of the Patriarchal Bogoyavlensky Cathedral.

After the death of Patriarch Alexis (April 1970) Pimen, Metropolitan of Krutitzy and Kolomna, in accordance with the Regulations of the Management of the Russian Orthodox Church, was locum tenens of Patriarch's see, and on June 2, 1971 the General Council of the Russian Orthodox Church elected him Patriarch of Moscow and All Russia.

Patriarch Pimen is an honorary member of the Moscow and Leningrad theological academies. He has been awarded the highest Order of the Russian Orthodox Church and Orders of Orthodox Churches of other countries. In 1972-1973 he officially visited the heads of the Alexandria (ARE), Jerusalem, Antioch (Syria and Lebanon), Ellas (Greece), Serbian (Yugoslavia), Bulgarian, Rumanian, Polish,-Czechoslovakian and Georgian Orthodox Churches, the Patriarch Catholicos of All Armenians and the headquarters of the World Council of Churches in Geneva.

In addition to Church activities Patriarch Pimen pays great attention to urgent problems of the present-day the struggle for peace on earth. Since 1963 Patriarch Pimen has been a Member of the World Council of Peace and the Soviet Peace Committee, and a Member of the Soviet Committee for Cultural Relations with Countrymen Abroad. He took part in the Warsaw (1963) and Geneva (1966) sessions of the World Council of Peace, in the World Congresses for Universal Disarmament and Peace in Moscow 1962 and in Helsinki (1965), the World Peace Assembly in Berlin (1969), the Assembly of the World Council of Peace in Budapest (1971) and finally, in the World Congress



of Poace Forces in Moscow in October 1973.

On the initiative of Patriarch Pimen the Russian Orthodox Church contributed 3 million roubles to the Soviet Peace Fund.

During his activities in the defence of peace Patriarch Pimen was awarded the gold medal "Peace Champion" and a medall of the Soviet Peace Fund engraved with his name.



www.ethiopianorthodox.org

# FROM THE HISTORY OF RELATIONS BETWEEN THE PEOPLES OF RUSSIA & ETHIOPIA

Specialists and the public know about the numerous Russian expeditions to Ethiopia starting from the late 19th century and the return visits of the Ethiopians to Russia. Few people know, however, that the relations between Ethiopia and the peoples of the Soviet Union—Russians, Ukrainians, Armenians, Georgians, Azerbaijanians and the peoples of Central Asia—date from long before the early 19th century.

The first information about Ethiopia came to these peoples from Greek literature, translated into the old Armenian, old Georgian and old Slav languages. The Armenian and Georgian translations of the book of Epiphanius, the Georgian translation of *The Road from Eden*, the translation of Cosmas Indicop,-leustes' book into the old Slav which was very popular in medieva Russia and the Ukraine, contain information about ithe Axumite Kingdom. From the Greek literature knowledge of Ethiopia made its way into original works in the old Armenian and old Slav languages.

The inhabitants of Central Asia and Azerbaijan and the Tatars of the Volga region learned about Ethiopia from the works of Arbaic and Persian literature. Arbabic was also known to many Armenians, who took a keen interest in the African country akin to them by religion.

At the close of the 12th century a book by the Armenian Abu-Salih came out in Arabic. It contained unique material on the Ethiopia of that time. Abu-Salih himself never visited Ethiopia, but learned about it in Egypt.


In the same century and Ethiopian community was founded in Palestine, composed of priests living permanently in Jerusalem and pilgrims to the "Holy Places". The Ethiopian kept up close relations with similar Coptic and Armenian community ,and also with the local Armenian merchants. Subsequently, the Armenians pledged officially to support the Ethiopians.

At the beginning of the 14th century direct relations were established between Ethiopia and the Armenians, on the initiative of the Ethiopians.

In the early 14th century the famous Ewostatewos (Eustathius), founder of a major social-religious movement in medieval Ethiopia, undertook a journey to the north: to Nubia, Egypt, Palestine, Cyprus and "Armenia", or to be more exact, the Armenian kingdom in Cilicia. In Alexandria Ewostatewos met the Armenian Patriarch and decided to visit Armenia without fail. He did settle down in the "Armenian land", died there and was presumably buried by the Patriarch himself.

His followers began to translate into the Geez language the lives of the Armenian "saints" and works attributed to them. At the close of the 16th century translations from the Arabic were made of the *Life of St. Gregory*, the patron of the Armenians, who converted them to Christianity; some theological works attributed to Gregory and fragments of the dogmatic work of *Euphraxius, Archbishop of Armenia* were also translated. Short lives of the Armenian martyrs, Phipsimia and Gayane, were translated from the Arabic into Geez. To this day the Ethiopian church observes the 19 and 30 of Maskaram and the 15 of Tahsas in honour of Gregory, and the 29 of Maskaram in honour of Phipsimia and Gayane.

*Ethiopian Students in Leningrad in Metropolitan Nikodim*







www.ethiopianorthodox.org